21/09/12 ዓ.ም

# ለሀዲስ አለማዬሁ ልዩ አዳሪ ት/ቤት የተዘጋጀ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወርክሽት

I. ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጭ፤

1. "አስቴር ፈጣን ሯጭ ነች።" በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል፣

   ሀ. ስም ለ. ግስ ሐ. ቅፅል መ. ተ/ግስ

2. ከሚከተሉት ውስጥ ቁጥር አመልካች ቅጥያ የተጨመረበት ቃል የቱ ነው?

   ሀ. እፅዋት ለ. ደግነት ሐ. ክብርት መ. ላሚቱ

3. ከሚከተሉት መካከል ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ከአንድ በላይ ፍች ያለው የቱ ነው?

   ሀ. ዳቦ ለ. ይመራል ሐ. ቀፎ መ. ሁሉም

4. በክርክር ጊዜ የክርክሩ ዳኖች ዋና ተግባር ፣ ሀ. ስርዓት ማስከበር ለ. አሸናፊና ተሸናፊን መለየት

   ሐ. ግልፅነት የሌላቸው ነጥቦችን ማብራራት መ. ሰዓት መቆጣጠር

5. ተመልካችን ከማሳዘንና ከማስጨነቅ ይልቅ እያሳቀ ቁምነገርን የሚያስጨብጥ የተውኔት አይነት፣

   ሀ. ትራጀዲ ለ. ኮሜዲ ሐ. ሜሎ ድራማ መ. ድንቃይ

6. ቀድሞ አለማሰብን /አለመዘጋጀትን/ የሚገልፀው ምሳሌያዊ ንግግር የቱ ነው?

   ሀ. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ለ. ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ ሐ. ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ

   መ. ከድጡ ወደ ማጡ

7. ሆዴ ባዶ ነው ____ የመመገብ ፍላጎት ግን የለኝም። በክፍት ቦታው ላይ የሚገባው ስርዓተ ነጥብ፣

   ሀ. ነጠላ ሰረዝ (፣) ለ. ድርብ ሰረዝ (፤) ሐ. ሁለት ነጥብ ከሰርዝ (፡-) መ. ክንፍ (())

8. በሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል የሚካሄድ ሙግት/ እሰጣገባ፣

   ሀ. ጭውውት ለ. ውይይት ሐ. ክርክር መ. ምልልስ

9. የአንድን ነገር ምንነት፣ባህርይ፣ ጠቀሜታ፣ወዘተ. በዝርዝር የሚገልፅና ዋና ዓላማው የንድፈ ሀሳብ እውቀት ማስጨበጥ የሆነ የድርሰት አይነት፣ ሀ. ተራኪ ለ. ገላጭ ሐ. ስዕላዊ መ. አመዛዛኝ

10. የሀሳብ አንድነት ያላቸው የስንኞች ስብስብ ምን ይባላል?

    ሀ.አርኬ ለ.ቀለም ሐ.ስንኝ መ. ቤት መድፊያ

11. "እያዩ  አለማየት" የሚለው አገላለፅ የቀረበበት ዘይቤ ፣

ሀ. ሰዎኛ   ለ. ለዋጭ   ሐ. አያዎ   መ. ምፀት

12. "ኦች" የሚለውን አብዢ ምዕላድ የማይቀበለው የስም አይነት፣

ሀ. የወል ስም   ለ. ተውላጠ ስም   ሐ. የቡድን መጠሪያ ስም   መ. ሁሉም

13." የትናንቱ ሽማግሌ ጠጅ ጠጥቶ ሰከረ።" በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ ተሳቢው፣

ሀ. የትናንቱ ሽማግሌ   ለ. ጠጅ   ሐ. ጠጥቶ   መ. ጠጥቶ ሰከረ

14. "ውረድ እንውረድ ተባባሉና፣

አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና" በሚለው ግጥም ውስጥ በሀረግ ያለው የቀለም ብዛት፣

ሀ. 6/6   ለ. 5/5   ሐ. 4/4   መ. 6/5

15. በልቦለድ ውስጥ የገሀዱን አለም ሰው ወክሎ የሚንቀሳቀስ ባለታሪክ ምን ይባላል?

ሀ. ተዋናይ   ለ. ገፀ ባህርይ   ሐ. ትልም   መ. መቼት

16. የገዛ ወገንን አንገት የመቅላት ____ ጀብዱ____ ትርጉሙ ምንድን ነው? በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ በክፍት ቦታው ላይ የሚገባው ስርዓተ ነጥብ፣

ሀ. ነጠላ ሰረዝ (፣)   ለ. ድርብ ሰረዝ (፤)   ሐ. ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ (" ")   መ. ክንፍ (())

17. ከሚከተሉት ውስጥ ከቅፅል የተመሰረተው ውልድ ስም የቱ ነው?

ሀ. ልጅነት   ለ. ቸርነት   ሐ. ክፉኛ   መ. ፈረሰኛ

18. "የስኬት ሁሉ ምንጩ ሁልግዜም ዕድል ስለመሆኑ ፍፁም አላምንም።" በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ፣   ሀ. ስም   ለ. ቅፅል   ሐ. ግስ   መ. ተ/ግስ

19. በቅኔ ውስጥ ሁለት አይነት ፍች የያዘው ቃል /ሀረግ ምን ይባላል?

ሀ. ሰም   ለ. ወርቅ   ሐ. ህብረቃል   መ. ሚስጢር

20. በተውኔት ውስጥ ታሪኩ የሚፈፀምበት ጊዜና ቦታ______ ይባላል።

ሀ. ትልም   ለ. ታሪክ   ሐ. መቼት   መ. ግጭት

21. "የአለሙ አባት የናጠጡ <u>ቱጃር</u> በመሆናቸው የተለያየ ሰበብ በመፍጠር የፖሊስ አዛዡ ከስር ቤት አስወጧቸው።" በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍች፣

ሀ. ጉልበተኛ   ለ. ሀብታም   ሐ. ነገረኛ   መ. ደሀ

22. የመተባበርን (ህብረትን) አስፈላጊነት የሚገልፀው ምሳሌያዊ ንግግር የቱነ ነው?

ሀ. ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ   ለ. ካንድ ብርቱ ሁለት መድሃኒቱ   ሐ. ሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ
መ. ሁሉም

23. "ሀኪሞቹ ሁሉ ሻይ ጥሩ ሲሉዎ፣

ወደ ቡን መጠጣት አደላ ልብዎ።" በሚለው ቅኔያዊ ግጥም ውስጥ ህብረቃሉ፣

ሀ. ሻይ   ለ. ወደ ቡን   ሐ. መጠጣት   መ. አደላ ልብዎ

24. "በተደረገለት ድጋፍ <u>ሆዱ ቅቤ ጠጣ</u>።"የተሰመረበት ፈሊጣዊ አገላለፅ ፍች፣

ሀ. ተሸማቀቀ   ለ. ተደሰተ   ሐ. ሆድ ባሰው   መ. ቂም ያዘ

25. በስንኝ መጨረሻ ላይ ያለው ቃል የመጨረሻ ሆሄ/ድምፅ ምን ይባላል?

ሀ. ቤት   ለ. ሐረግ   ሐ. ቤት መምቻ   መ. ቤት መድፊያ

26. "ራሳችንን ከኮሮና ቫይረስ ከምንከላከልባቸው መንገዶች አንዱ ንፅህናን መጠበቅ ነው፤------------- እያንዳንዳችን በተወሰኑ ሰዓታት ልዩነት እጃችንን ለ20ሰከንድ በሳሙና በደንብ መታጠብ ይኖርብናል።"

በክፍት ቦታው ላይ ሊገባ የሚችለው አያያዥ ቃል፣

ሀ. ይሁን እንጅ   ለ. ቢሆንም   ሐ. ሆኖም   መ. ስለዚህ

27. የደብዳቤው የመግቢያ ክፍል "ጉዳዩ" በሚል የሚገለፅበት የደብዳቤ አይነት፣

ሀ. የሰላምታ ደብዳቤ   ለ. የስራ ደብዳቤ   ሐ. የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ   መ. የፍቅር ደብዳቤ

**II. አጭርና ግልፅ መልስ ስጥ/ጭ፤**

28. "ቤት እሰራ ብዬ ተሳነኝ ጉልበቴ፣

አለም አገር ቀረች ዋ! ቤቴ ዋ! ቤቴ።" የሚለውን ቅኔያዊ ግጥም ህብረ ቃል፣ ሰም ና ወርቅ አውጣ/ጭ።

ህብረ ቃል= ______________________________________________

ሰም=____________________________________________________

ወርቅ=__________________________________________________

29. ክርክር ከጭውውትና ውይይት የሚለይባቸውን ቢያንስ ሁለት ነጥቦችን ጥቀስ/ሽ።

ሀ. ____________________________________________________________________

ለ. ____________________________________________________________________

30. የሚከተሉትን ቃላት መሪ በማድረግ ሀረግ መስርት/ች፡፡

ሀ. ደግ=________________________________________

ለ. ቤት=________________________________________

ሐ.መለኛ=_______________________________________

መ. ወደቀ=______________________________________

ሠ. ክፉኛ=_______________________________________

ረ. ከ…ውስጥ=____________________________________

31. የሚከተሉትን ቃላት እማሪያዊና ፍካሪያዊ ግለፅ/ጭ፡፡

| | <u>እማሪያዊ ፍች</u> | <u>ፍካሪያዊ ፍች</u> |
|---|---|---|
| ሀ. መሰላል | __________ | __________ |
| ለ. ሙቅ | __________ | __________ |
| ሐ. እሳት | __________ | __________ |
| መ. ቀበሮ | __________ | __________ |
| ሠ. እሾህ | __________ | __________ |
| ረ. አኖ | __________ | __________ |

32. "የትናንቱ ልጅ በመኪና አደጋ ህይወቱን አጣ፡፡" የዚህን ዓ/ነገር ስማዊና ግሳዊ ሀረግ አውጣ/ጭ፡፡

ሀ. ስማዊ ሀረግ=________________________________________

ለ. ግሳዊ ሀረግ=________________________________________

33. የሚከተሉት ግጥሞች የቀረቡበትን የዘይቤ አይነት ግለፅ/ጭ፡፡

ሀ. ወፎች ተጠሩሩ ነውና መምሸቱ፣

ወደየጎጇቸው ገብተው ሊከተቱ፡፡"

ለ. "ወትሮም ካንጀቴ አይደል እሱን መጠጋቴ ፣

አውሬ መሳዩን ሰው ሙጥኝ ማለቴ፡፡"

ሐ. “ጀንበር ነሽ አበባ ሕይወት ተስፋ ዘቦ፣

ፋሲካ እንቁጣጣሽ ማህሌተ ገንቦ፡፡”

መ. “ትርንጎ ነሽ አሉ የምትገመጭ ፣

ከልቤ ገብተሻል አርፈሽ ተቀመጭ፡፡”

ሠ. “እህል ዱር አደረ ብቻውንም ዋለ፣

ጠላት እንደሌለው ሰው እንዳልገደለ፡፡”

**“ራሳችንን ከኮሮና ቫይረስ እንጠብቅ፤ ትምህርታችንን በቤታችን ሆነን እንከታተል!!!”**